በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የትራንስፖርት ቢሮ

ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
TRANSPORT BUREAU

# የኤሌክትሮኒክ የታክሲ ስምሪት (የኤታስ) አገልግሎት አሰጣጥ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 05/2011

ነሓሴ 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የከተማዋን የታክሲ አገልግሎት በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ፍትሃዊ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል፤

የትራንስፖርት አገለግሎቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሠራር በመደገፍ ዘርፉን ለማዘመንና ምቹ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ወሳኝ በመሆኑ፤

የቴክኖሎጂ እድገትን ተከትሎ የሚመጡ አዳዲስ ፍላጎቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ወሳኝ በመሆኑ፤

የከተማዋ የታክሲ አገልግሎት በማቀናጀ ቴክኖሎጂ የመጠቀም ፍላጎት እያደገ በመምጣቱና ይህም በአጠቃላይ የትራንስፖርት አገልግሎቱም ሆነ በኢንዱስትሪው ውስጥ አወንታዊ ተጽዕኖ እንዲኖረው የአሠራር ስርዓት በመዘርጋት ምህዳሩ ምቹ እንዲሆን አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከተማዋ የትራንስፖርት መረጃ ትስስር መተግበሪያ ስርዓቶችን በመጠቀም የታክሲ ፍላጎትና አቅርቦት መረጃ ለአገልግሎት ፈላጊውንና አገልግሎት ሰጪውን በማቅረብ የተሰማሩ ተቋማትና ግለሰቦች ወደ ገበያው እየገቡ ከመሆኑ አንጻር ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ለማስቀረትና ነፃ ውድድር መፍጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስተዳደራዊና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን እንደገና ለማደራጀት በወጣው አዋጅ ቁጥር **64/2011** አንቀጽ **15** ንዑስ አንቀጽ **3(ሠ)** መሠረት የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት አድርጎ ይህን የአሰራር መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ *"በኤሌክትሮኒክ የታክሲ ስምሪት (የኤታስ) አገልግሎት አሰጣጥ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 05/2011"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

**2.1.** **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው።

**2.2.** **"ቢሮ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ነው።

**2.3.** **"ባለስልጣን"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ባለስልጣን ነው።

2.4. **"ማህበር"** ማለት በአገሪቱ የንግድ ህግ መሠረት የታክሲ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የወሰዱ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ወይም ኦፕሬተሮች የጋራ ዓላማቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር ያቋቋሙት ማህበር ማለት ነው።

2.5. **"ኤታስ"** ማለት ኤሌክትሮኒክ የታክሲ ስምሪት ማለት ነው።

2.6. **"የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ግለሰብ"** ማለት ይህ መመሪያ በሚጠይቀው መስፈርት መሠረት የኤታስ መተግበሪያ በመጠቀም የታክሲ ስምሪት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ውስጥ ተመዝግቦ የታክሲ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያወጣ ነገር ግን በማህበር ሳይመዘገብ በግሉ የታክሲ አገልግሎት የሚሰጥ የተሽከርካሪ ባለቤት ወይም አሽከርካሪ ማለት ነው።

2.7. **"የኤሌክትሮኒክ ስምሪት ስርዓት"** ማለት የመረጃ መረብን በመጠቀም የታክሲ አገልግሎቶችን በማስተሳሰር የታክሲ አገልግሎት ፈላጊዎችንና የታክሲ አገልግሎት ሰጪዎችን ለማገናኘት ጥቅም ላይ የሚውል የመተግበሪያ ቴክኖሎጂ ነው።

2.8. **"የጥሪ ማዕከል"** ማለት የኤታስ ስምሪት መተግበሪያ ስርዓትን በመጠቀም የታክሲ አገልግሎት ፈላጊውንና የታክሲ አገልግሎት ሰጪዎችን የሚያገናኙ ድርጅቶች በነፃ ወይም በክፍያ በሚሰራ ስልክ በመጠቀም በኦፕሬተሮች ወይም በሌሎች አማራጭ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ተገልጋዩንና አገልግሎት ሰጪውን የሚያገናኙበት ማዕከል ነው።

2.9. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የኤሌክሮኒክ ስምሪት መተግበሪያ ስርዓትን በመጠቀም የታክሲ አገልግሎት የማሰማራት ስራ የሚያከናውኑ ድርጅቶች እና በኮድ-1 የተመዘገቡ የታክሲ አገለግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች፣ የታክሲ ማህበራት እና ግለሰብ የታክሲ አገልግሎት ሰጪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት
# የኤታስ አገልግሎት ፍቃድ፣ መስፈርቶች እና ግዴታዎች

## 4. የኤታስ አገልግሎት ፍቃድ

4.1 ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በኮድ-1 የተመዘገቡ የታክሲ አገለግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች በመመዝገብ የኤሌክትሮኒክ ታክሲ ስምሪት አገልግሎት መስጠት የተፈቀደ ሲሆን ይህንን ተግባር ለማከናወን ከባለስልጣን መ/ቤት የኤታስ አገልግሎት ሰጪ ልዩ ፍቃድ ማግኘት ይገባል።

4.2 በባለስልጣኑ ልዩ ፍቃድ የተሰጣቸው በኤሌክትሮኒክ የታክሲ ስምሪት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በመመዝገብ የታክሲ አገልግሎት ለመስጠት ፍቃደኛ የሆነ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የታክሲ አገልግሎት ለመሰማራት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች በሟሟላት ተሽከርካሪው በኮድ-1 በመመዝገብ የታክሲ አገለግሎት መስጠት ይችላል፡፡

## 5. የኢታስ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

5.1 በኢታስ አገልግሎት ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት የኢታስ ስርዓት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ እና የአገልግሎት መስጫ ልዩ ፈቃድ ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ማግኘት ይችላል፡፡

i. የኢታስ ስርዓት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ማውጣት አለበት፤

ii. የኢታስ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ የኢታስ መተግበሪያ መሠረተልማት እና የመረጃ ቋት (database) በአገር ውስጥ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

iii. የኢታስ የመተግበሪያ ስርዓቱን ምንነትና ዝርዝር መግለጫ እንዲሁም የንግድ ዝክረ ሃሳብ ለባስስልጣን መስሪያ ቤቱ በሰነድ ማቅረብ አለበት፤

iv. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለኢታስ አገልግሎት መስጫ የተደራጀ ቢሮ መክፈት አለበት፤

5.2 በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት መስፈርቶች በፈቃድ እድሳት ወቅትም የሚያገለግሉ ይሆናል።

## 6. በኢታስ ስርዓት አማካኝነት የታክሲ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተሽከርካሪዎች መስፈርቶች

6.1. የተሽከርካሪ የሲሲ መጠን፣ የመንገደኞች (ተሳፋሪዎች) ብዛት፣ የቀለም ዓይነት እና ሌሎች መሰል ቴክኒካል መስፈርቶች በትራንስፖርት ባለስልጣን ደረጃ (ስታንዳርድ) መሰረት ያሟላ ተሽከርካሪ መሆን አለበት።

6.2. በኢታስ መተግበሪያ ስርዓት ውስጥ በመመዝገብ የታክሲ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት በኮድ-1 የታክሲ አገልግሎት የተመዘገቡና ፈቃድ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ብቻ ናቸው።

6.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **6.2** የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢታስ መተግበሪያ ስርአት አገልግሎት ሰጪ ጋር ቢያንስ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የግዴታ ውል መግባት አለባቸው።

6.4. ተገልጋዩ በቀላሉ ሊለያቸው የሚችል ቀለም ነጭና ሰማያዊ ወይም የማህበራቸው ሎጎ ያለበት ቢጫ በአረንጓዴ መቀባት አለበት።

6.5. ተገቢውን ዓመታዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ያለው መሆን አለበት።

6.6. አስፈላጊ የሆኑ የተሽከርካሪና የሦስተኛ ወገን ኢንሹራንሶችን አሟልቶ የገባና ያደሰ መሆን አለበት።

6.7. ተገቢውን ወቅታዊ ግብር የከፈለና ማረጋገጫ ያለው መሆን አለበት።

## 7. የኢታስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ግዴታዎች

7.1 በኢታስ መተግበሪያ ስርዓቱ መዝግበው የሚያሰሯቸውን አሽከርካሪዎች ስም፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ፎቶ፣ የመንጃ ፈቃድ መረጃዎች ከነፎቶው ጨምሮ የአሽከርካሪውን ሙሉ መረጃ በመተግበሪያ ስርዓቱ ላይ መመዝገብ አለበት።

7.2 በኢታስ መተግበሪያ ስርዓቱ መዝግበው የሚያሰሯቸውን ተሽከርካሪዎች ስሪት፣ ሞዴል፣ ፎቶ፣ የታርጋ ቁጥርን ጨምሮ የተሽከርካሪዎችን ሙሉ መረጃ በመተግበሪያ ስርዓቱ ላይ መመዝገብ አለበት።

7.3 የኢታስ የመተግበሪያ ስርዓቱን ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ (read only access) ክፍት ማድረግና ቀጥታ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ማድረግ አለበት።

7.4 በባለታክሲው ወይም በአሽከርካሪው ተገቢውን አገልግሎት ለተገልጋዩ መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት።

7.5 በኤታስ የመተግበሪያ ስርዓቱ ተካተው የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች ተገቢውን የብቃት ማረጋገጫና አስፈላጊ ፈቃድ እንዲሁም በአገሪቱ የተሽከረካሪና የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንሶች የገባና የታደሰ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

7.6 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በመተግባሪያ ስርዓቱ ገብተው መስራት ስለሚችሉ ተሽከርካሪዎች የተዘረዘሩ መስፈርቶች ሁሉ መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

7.7 መዝግበው ለሚያሰሯቸው አሽከርካሪዎች ተገቢውን የስነ-ምግባር ስልጠና መስጠት አለበት።

7.8 የአሽከርካሪዎችን እና የተሽከርካሪዎችን ሙሉ መረጃ (የአሽከርካሪው፣ ተሽከርካሪው ሁኔታ፣ የተገልጋዮች ጥሪ፣ የተጓዘበት መንገድ፣ ሰዓት እና መሰል መረጃዎች) በመተግበሪያ ስርዓቱ ላይ ቢያንስ ለአንድ ዓመት መያዝ ግዴታ አለበት።

7.9 በማንኛውም ባስፈለገ ጊዜ የእያንዳንዱን ተሽከርካሪ ዝርዝር መረጃ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱና ለሌሎች የመንግስት ተቋማት መስጠት አለበት።

7.10 ተገልጋዮችን በአገልግሎት አሰጣጡ ከምንም ዓይነት ጉዳትና እንግልት እንዲሁም ከማንኛውም ህገ-ወጥ ተግባር የመጠበቅና ደርሶባቸው ሲገኝም መረጃውን ለሚመለከተው የመንግስት ተቋም የማሳወቅ እና ተገቢውን ካሳ የመስጠት ግዴታ አለበት።

7.11 ተገልጋዮች ተሽከርካሪው ውስጥ ከመግባታቸው አስቀድሞ የሚከተሉትን መረጃዎች በቀጥታ የመስጠት ግዴታ አለበት፡-

i. የአሽከርካሪውን ስም እና ፎቶ ግራፍ መስጠት አለበት፤
ii. የተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር እና የጎን መለያ ቁጥር መስጠት አለበት፤
iii. የአገልግሎት የታሪፍ መጠን ወይም ሌሎች አማራጭ የክፍያ ስሌቶችን ማሳወቅ አለበት።

7.12 የኤታስ መተግበሪያ ስርዓትን በመጠቀም አገልግሎት የሚሰጥ አሽከርካሪ ማንኛውንም አልኮል ወይም አደንዛዥ ዕጽ ወስዶ የታክሲ አገልግሎት መስጠት በፍፁም የተከለከለ መሆኑን በየጊዜው የማሳወቅና አሰራሩን ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

7.13 ማንኛውም የኤታስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለአሽከርካሪዎቹ የታሪፍ ስሌቶችን ወይም ሌላ ተገቢ የሆነ የክፍያ መጠን መገመቻ አማራጮችን አዘጋጅቶ መስጠትና ማስተግበር አለበት።

7.14 ማንኛውም የኤታስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በዚህ መተግበሪያ አማካኝነት የተደረገ እያንዳንዱ አገልግሎት ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን መረጃዎች በቀጥታ በመተግበሪያ ስርዓቱ ላይ መዝግቦ መያዝ ይኖርበታል።

i. የጉዞው መነሻና መድረሻ ቦታ፤
ii. የጉዞው ርቀትና ጉዞው የፈጀው ጊዜ፤
iii. የመነሻ ታሪፍን ጨምሮ ተጓዡ ለጉዞው የከፈለው አጠቃላይ የክፍያ መጠን።

7.15 ለመደበኛ የታክሲ ተገልጋይ በባለስልጣኑ ታሪፍ መሰረት የማስከፈል ግዴታ ያለበት ሲሆን በልዩ ሁኔታ በቅድመ አገልግሎት በሚደረግ ስምምነት ግን የአገልግሎት ታሪፍ በተዋዋዮች ሊወሰን ይችላል።

7.16 በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት የሚከሰቱ የወንጀል ድርጊቶች ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት።

## 8. የባለስልጣን መ/ቤቱ ሃላፊነትና ተግባር

8.1. በዚህ መመሪያ መሠረት ተገቢውን የብቃት ማረጋገጫ ለሚያቀርቡና ሌሎች መስፈርቶች ያሟሉ ድርጅቶች እና ግለሰቦች መርምሮ ፈቃድ መስጠትና ማደስ፤

8.2. በመመሪያው መሠረት ተገቢውን ቁጥጥርና ድጋፍ ማድረግ፤

8.3. በዚህ መመሪያ መሠረት ከህግ ውጭ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችና አሽከርካሪዎች እንዲሁም ማህበራት እና ግለሰቦች ላይ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ መውሰድ።

# ክፍል ሦስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 9. የተከለከሉ ተግባራት

የኤታስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን የማይፈቀድለት ሲሆን ድርጊቶቹን ተላልፎ ሲገኝ ለቅጣት ይዳረጋል፡-

9.1. ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ካወጣው ታሪፍ በላይ ማስከፈል የተከለከለ ነው።

9.2. የኤሌክትሮኒክ ታክሲ ስምሪት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ድርጅት በተመሳሳይ ፈቃድ የራሱን ታክሲዎች ገዝቶ ወይም ተከራይቶ መስራት የተከለከለ ነው።

9.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **9.2** የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለታክሲ አገልግሎት እራሱን የቻለ ፈቃድ በማውጣትና የኤታስ መተግበሪያ ስርዓቱን በመጠቀም አገልግሎት መስጠት ይችላል።

9.4. በባለስልጣኑ እውቅና የሌለውና ፍቃድ ያልተሰጠበት የኤታስ የመተግበሪያ ስርዓት መጠቀም የተከለከለ ነው።

9.5. ማንኛውንም በዚህ መመሪያ ከተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች ውጭ መዝግቦ የታክሲ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ የተከለከለ ነው።

9.6. በዚህ መመሪያ መሰረት መረጃን ለባለስልጣን መ/ቤቱ ወይም ለሚመለከተው የመንግስት ተቋም አለመስጠት የተከለከለ ነው።

9.7. ለባለስልጣን መስሪያቤቱ የኤታስ የመተግበሪያ ስርዓት ክፍት አለማድረግና የቴክኖሎጂው ይለፍቃል (password) አለመስጠት ወይም በከፊል መረጃ የሚያሳይ ማድረግ የተከለከለ ነው።

## 10. የቅጣት ሰንጠረዥ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ **9** ላይ የተዘረዘሩትን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም የኤታስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በሰንጠረዥ-**1** የተገለፁት ቅጣቶች ተግባራዊ ይደረጉበታል፡፡ በታክሲ አሽከርካሪ በሌሎች የትራንስፖርት ህጎች መሠረት የሚፈጸም ይሆናልሚፈጸሙ የትራፊክ እና የትራንስፖርት ደንብ ጥሰቶች በሌሎች የትራንስፖርት ህጎች መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

**ሰንጠረዥ 1.** *የኤታስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የቅጣት መጠን።*

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት | የጥፋቱ ድግግሞሽና የቅጣት መጠን (በብር) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ለመጀመሪያ ጊዜ | ለሁለተኛ ጊዜ | ከሁለት ጊዜ በላይ |
| 1 | ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ካወጣው ታሪፍ በላይ ማስከፈል፤ | መተግበሪያ ስርዓት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ላይ | | |
| | | 1,000 | 2,000 | 3,000 ብር ተቀጥቶ የመተግበሪያ ስርዓት አገልግሎት የሚሰጠው ድርጅት ፈቃድ ለስድስት ወር ይታገዳል፤ የአሽከርካሪው መንጃ ፈቃድ ለ 1 ወር ይታገዳል። |
| 2 | የኤሌክትሮኒክ ታክሲ ስምሪት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ድርጅት በተመሳሳይ ፈቃድ የራሱን ታክሲዎች ገዝቶ ወይም ተከራይቶ መስራት፤ | 3,000 | 6,000 | 10,000 ብር ተቀጥቶ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ይደረጋል። |
| 3 | በባለስልጣኑ እውቅና የሌለውና ፍቃድ ያልተሰጠበት የኤታስ የመተግበሪያ ስርዓት መጠቀም | ፈቃድ የሌለው ከሆነ ስራው የሚታገድ ሲሆን በሌላ መተግበሪያ ፈቃድ ወስዶ እየሰራ ያለ ከሆነ በቀጥታ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ይደረጋል። | | |
| 4 | ማንኛውንም በዚህ መመሪያ ከተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች ውጭ መዝግቦ የታክሲ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ | 3,000 | 6,000 | 10,000 ብር ተቀጥቶ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ይደረጋል። |
| 5 | መረጃን ለባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ አለመስጠት | 4000 | 8000 | 15,000 ተቀጥቶ የድርጅቱ ፈቃድ ለ3 ወር እንዲታገድ ይደረጋል። |
| 6 | የመተግበሪያ ስርዓቱን የይለፍ ቃል (Password) ለባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ክፍት አለማድረግና ያለባለስልጣኑ እውቅና የይለፍ ቃል ቀይሮ መጠቀም | 3,000 | 6,000 | የድርጅቱ ፈቃድ በቀጥታ የሚታገድ ይሆናል። |

## 11. የቅሬታ አቀራረብ

11.1 በአንቀጽ 10 መሠረት ቅጣት የተላለፈበት እና በተላለፈበት ቅጣት ተገቢነት ወይም በማንኛውም ተያያዥ ጉዳይ ላይ ቅሬታ ያደረበት ማንኛውም አካል፡-

i. በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለስልጣን መ/ቤቱ በፅሁፍ ለማቅረብ ይችላል።

ii. ባለስልጣን መ/ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ በአምስት ቀናት ውስጥ መርምሮ ምላሽ መስጠት አለበት።

iii. በባለስልጣን መ/ቤቱ ውሳኔ ተገቢነት ላይ ቅሬታ ያደረበት ወይም ባለስልጣን መ/ቤቱ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ባለስልጣን መ/ቤቱ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ወይም ውሳኔ መስጠት ከነበረበት ቀን አንስቶ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቢሮ ማቅረብ ይችላል።

iv. ቢሮው የቀረበለትን ቅሬታ በሰባት ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት።

v. የቢሮው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።

11.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ **11.1** ከ"**i—iii**" በተደነገገው መሠረት ቅሬታውን አቅርቦ ቅጣቱን ካላሻረ በስተቀር የተጣለበትን ቅጣት በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ መክፈል ይኖርበታል።

11.3 ቅጣቱን በ**አስር** የሥራ ቀናት ያልከፈለ ሰው ከ**11ኛው** ቀን ጀምሮ በ**የቀኑ** ከዋናው ቅጣት **5** በመቶ ተጨማሪ እየተሰላ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 12. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የሚመለከተው አካል ይህ መመሪያ በአግባቡ እንዲፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

## 13. ስለተጠያቂነት

ይህን መመሪያ የሚያስፈፅም ማንኛውም ሰው በሚያከናውናቸው ተግባራት የተሰጠውን ሃላፊነት ተላልፎ ቢገኝ የሚወሰድበት አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ህግም ሊጠየቅ ይችላል።

## 14. መመሪያዉን ማሻሻል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል።

## 15. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሓሴ **24፣ 2011** ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ

ነሓሴ **24** ቀን **2011**ዓ.ም.

ሰለሞን ኪዳኔ ዘገየ (ፒ.ኤች.ዲ.)

የአዲስ አበባ ከተማ ኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪና

የትራንስፖርት ቢሮ ሀላፊ